# አባይም ይከሰስ!

የማመልከቻ አይከፍል፥ የፓስፖርት የቪዛ፥
አባይ አገር ለቆ ሲነጉድ እንደዋዛ፡፡

ዘመድ ቀረኝ አይል እናቴና አባቴ፥
ወንድም፥ እህቶቼ፥ አጎቴና አክስቴ፤
ወይ! ወገኔ! አላለ ወይ! እናት አገሬ!
በትናቸው ሲሄድ እያለ "አውጪኝ እግሬ"

ያለ የሌለውን ዘርፎ ከናት ጓዳ፥
ጥርግ አርጎ ወስዶ ሲያፈሰው ለባዳ፤
የሱም ጉድ ይውጣና እንደኛ ይወቀስ፥
በህግ ጠይቁልኝ አባይም ይከሰስ፡፡

ከጣና ተነስቶ ታቹን ሲያሽቀለቁል፥
እንዳፈኗት በቅሎ ሽምጥ ሲፈልል፥
ጠላት የሚያባርር መስሎ ፈረሰኛ፥
እንዳገሬ ጎበዝ እንዳገሬ አርበኛ፥
ጋራ ተራራውን ሽለቆውን ጥሶ፥
አረፋውን ሲደፍቅ ወደሰማይ ጨሶ፥
አንዴ ሲያጉረመርም አንዴ ሲያገሳ፥
እንደመቱት ደቦል የቆሰለ አንበሳ፥
ያዙኝ! ልቀቁኝ! ሲል ሲደነፋ በኛ፥
ይሉኝን የማያውቅ ፋይዳ ቢስ ጉረኛ፡፡

ድንበር እየጣሰ ትቶ መንደርደሩን፥
ምነው ዘወር ብሎ ቢያስባት አገሩን?

አይ! አባይ ጉደኛው!

አገሬን አቋርጦ ሲሰብር ኬላውን፥
አባይን አየሁት ለውጦ ጠባዩን፡፡
ገረመኝ! ደነቀኝ! ፍሬ ቢስነቱ፥
ለጠላት ለባዕድ አገልጋይነቱ፡፡
መንገዱን ቀይሰው "በል ከዚህ ቁም!" ሲሉት፥
አንዴ ወደቀኝ፥ ግራ ሲመልሱት፥
ለጥ ሰጥ፥ ብሎ አየሁ ሲንቀጠቀጥ፥
እጆቹን ዘርግቶ አባይ ሲለማመጥ፡፡

ጉራ በኪሱ አባይ ድንፋታውን ይተው፥
ጥርግ ብሎ ይሂድ እኔም አላግተው፥

ግን ካገር መዝረፉን ብዝበዛውን ይተው፡፡
ተመለስ አትበሉት ይሂድ አትከልክሉት፥
መንገዱ ጨርቅ ይሁን ሆ! ብላችሁ ሸኙት፡፡

መለስ! ቀለስ ብሎ አይጠቅመንም ለኛ፥
እንደወጣ ይቅር አይምጣ ዳግመኛ፡፡

ይፍሩ ኃይሉ
ኒው ሄቨን፥ ኮነክቲከት
ሰሜን አሜሪካ